በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የ ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ሰበር ሰሚችሎት

የመ.ቁ. 196174
መስከረም 28/2014 ዓ.ም

ዳኞች፡ እትመት አሰፋ

ፀሐይ መንክር

ኑረዲን ከድር

መላኩ ካሳዬ

እስቲበል አንዱዓለም

አመልካች፡ አቶ ጋትዴት ኛቾም የቀረበ የለም

ተጠሪ፡ አቶ ኒያል ደጆክ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍርድ

በዚህ መዝገብ ላይ የቀረበው ጉዳይ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ክርክርን የሚመለከት ሲሆን የተጀመረውም የአሁን ተጠሪ ጥር 05/2012 ዓም ፅፈው በጋምቤላ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ ተጠሪ ለፍርድ ቤቱ አቅርበዉ የነበረው ክስ ጭብጥም ለአስር ተከታታይ ዓመታት በእጃቸው አድርገው ሲገለገሉበት የነበረውን ይዞታ የአሁን አመልካች በራሳቸው ሥልጣን ይዘውባቸው ቤት የሰሩበት መሆኑን በመግለፅ በፍርድ ኃይል ሁከቱ ተወግዶ ይዞታው እንዲለቀቅላቸው ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

በዚሁ ክስ ላይ መልስ እንዲሰጥ በታዘዘው መሰረት አመልካች ክስ የቀረበበት ይዞታ በከተማው ማስተር ፕላን ምክንያት በተወሰደብኝ ይዞታ ምትክ በከተማው አስተዳደር ተሰጥቶኝ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ጭምር ወስጄበት የያዝኩት ይዞታዬ በመሆኑ ክሱ ውድቅ ሊደረግ ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ከሰማ በኋላ በሰጠው ውሳኔ ክስ የቀረበበት ይዞታ የአሁን ተጠሪ ስለመሆኑ ተጠሪው ባቀረቧቸው የሰው ምስክሮች የተረጋገጠ መሆኑን፣ በአሁን አመልካች በኩል የቀረቡ ምስክሮች ደግሞ ይዞታ የከተማ አስተዳደሩ የቀበሌ 01 ምክር ቤት በኩል የተሰጣቸው እንደሆነ መናገራቸውን፣ ሆኖም የቀበሌ ምክር ቤት የከተማ ይዞታን ለመስጠት ሥልጣን ያልተሰጣቸው መሆኑን፣ አመልካች በማስረጃነት ያቀረቡት የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትም በክርክር ሂደት የተሰጠ በመሆኑ ህገ ወጥ ነው በማለት የአመልካችን መከራከሪያ ውድቅ አድርጎ ይዞታውን ለተጠሪ ሊለቁ ይገባል ብሏል፡፡

ይህንኑ ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የጋምቤላ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በበኩሉ ክስ በቀረበበት ይዞታ ላይ ለአሁን አመልካች የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ቀርቦ እያለ ይህ ወደ ጎን ተደርጎ በሰው የምስክርነት ቃል ብቻ አመልካች ይዞታውን እንዲለቁ መወሰኑ አግባብ አለመሆኑን ተችቶ የስር ፍ/ቤትን ውሳኔ ሽሯል፡፡ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ደግሞ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱን ውሳኔ በመሻር የወረዳ ፍርድ ቤት ውሳኔን አጽንቷል፡፡ አመልካች በዚሁ ውሳኔ ላይ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ተቀባይነት አላገኘም፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንን ውሳኔ በመቃወም ነው፡፡ አመልካች መስከረም 15/2013 ዓ.ም  በተጻፈ የሰበር አቤቱታ በክልሉ የበላይ ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ ለክርከሩ ምክንያት የሆነው ይዞታ የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር ለአመልካች የሰጠው መሆኑን በስር ፍ/ቤት ውሳኔ በተገለፀበት ሁኔታ አመልካች ሁከት ፈጥረዋል በማለት የተሰጠውን ውሳኔ አግባብነት ከፍ/ህ/ቁ 1149 አኳያ በዚህ ሰበር ችሎት እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ የፅሁፍ ክርክር እንዲለዋወጡ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገበዋል ተብሎ የተያዘውን ነጥብ ከግራ ቀኙ ክርክር፣ ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

እንግዲህ ከክርክሩ አጀማመር መረዳት እንደሚቻለው ተጠሪ ያቀረቡት ክስ ለአስር ተከታታይ ዓመታት በእጄ አድርጌ ስለገለግለብት የነበረውን ይዞታዬን አመልካች በሥልጣኑ ይዞት ቤት የሰራበት በመሆኑ ሁከቱ ተወግዶ ይዞታው ሊለቀቅልኝ ይገባል የሚል ነው፡፡ የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለአንድ ንብረት ባለይዞታ ንብረቱን አስመልክቶ በህግ ከተረጋገጡት መብቶች ውስጥ አንዱ ስለመሆኑ የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149(1) ይደነግጋል፡፡ በዚህ መልኩ ክስ የሚያቀርብ ሰው ማረጋገጥ የሚጠበቅበት ዋና ዋና ፍሬ ነገሮች ሁከት ተፈጠረበት የተባለውን ንብረት/ሀብት/ ባልተቌበረበረ መንገድ በእጁ አድርጎ በእውነት የሚያዝበት መሆኑን እና በዚሁ ይዞታው ላይ በተከሰሰው ሰው ህገ ወጥ በሆነ መንገድ ሁከት የተፈጠረበት ስለመሆኑ ከፍ/ብ/ህ/ቁ/1140፣ 1146 እና 1149 ድንጋጌዎች ጣምራ ንባብ መረዳት ይቻላል፡፡ በዚህ አግባብ በቀረበ ክስ ላይ ሁከት ተፈጥሯል ተብሎ ውሳኔ የሚሰጠውም የተከሰሰው ሰው የሌላ ሰው ይዞታ መያዙ አልያም በይዞታው ላይ ሁከት መፍጠሩ ሲረጋገጥ እና የሁከት ክስ የቀረበበት አካልም የሥራውን አደራረግ የሚፈቅድ ለእርሱ የሚናገርለት መብት መኖሩን በፍጥነት እና በማይታበል ዓይነት ሁኔታ ሳያስረዳ ሲቀር ስለመሆኑ ከዚሁ ድንጋጌ ንዑስ ቁጥር 1 እና 3 ይዘት መረዳት ይቻላል፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ ተጠሪ ያቀረቡትን የሁከት ይወገድልኝ ክስ ለማስረዳት ያቀረቡት የሰው ምስክር ብቻ ነው፡፡ የተሰሙት ምስክሮችም ቢሆኑ ይዞታው የተጠሪ ነው የሚል የምስክርነት ቃል ከመስጠታቸው ባለፈ ለክርክሩ ምክንያት የሆነውን ይዞታ ተጠሪ በእጃቸው አድረገው በእውነት እያዘዙበት እያለ አመልካች በሁከት ተግባር የያዙባቸው ስለመሆኑ ያረጋገጡት ነገር የለም፡፡ በአንፃሩ የአሁን አመልካች በዚሁ ይዞታ ላይ የተሰጣቸውን የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እና ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ግብር ሲገብሩበት የነበረውን ማስረጃ ስለማቅረባቸው ከስር ፍርድ ቤት የመዝገብ ይዘት መረዳት

ማስታወሻ፡ - ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

ይቻላል፡፡ በእርግጥ አመልካች ያረቀቡት የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ግራ ቀኙ በክርክር ላይ እያሉ የተሰጠ ነው በሚል ውድቅ ተደርጓል፡፡ ሆኖም የይዞታ ማረጋጫ ምስክር ወረቀቱ ለአመልካች የተሰጠው ህዳር 03/2012 ሲሆን ተጠሪ ክስ ያቀረቡት ደግሞ ጥር 05/2012 ዓ.ም ስለመሆኑ የስር ፍርድ ቤት መዝገብ የሚያሳይ በመሆኑ ማስረጃው በክርክር ሂደት የተገኘ ነው የሚባል አይደለም፡፡ በክርክር ሂደት የተገኘ ነው ቢባል እንኳን ማስረጃው የተሰጠው ከህግ እና የአሰራር ደንብ ውጭ ስለመሆኑ እስካልተረጋገጠ ድረስ ውድቅ የሚደረግበት የህግ አግባብ የለም፡፡

ሲጠቃለል ተጠሪ ለክሱ መነሻ የሆነውን ይዞታ በእጃቸው አድርገው በእውነት እያዘዙበት እያለ በአሁን አመልካች በሁከት ተግባር የተያዘባቸው ስለመሆኑ ባልተረጋገጠበት፤ ይልቁንም አመልካች በይዞታው ላይ ቢያንስ ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ ግብር እየገበሩበት ያለ እና በይዞታው ላይም ሥልጣን ባለው አስተዳደር አካል የተሰጠ የይዞታ ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ያላቸው ስለመሆኑ ተረጋግጦ እያለ አመልካች በይዞታው ላይ ሁከት ፈጥረዋል ተብሎ እንዲለቁ መወሰኑ በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያላደረገ እና የፍ/ብ/ህ/ቁጥር 1149 ድንጋጌን መሰረታዊ ይዘት ያላገናዘበ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈፀመበት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

## ውሳኔ

1. የጋምቤላ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በፍ/ፋ/መ/ቁ/02517/2012 ላይ ሐምሌ 28/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ፤ የክልሉ ሰበር ሰሚ ችሎት ይህንኑ ውሳኔን በማፅናት የሰጠው ትዕዛዝ እንዲሁም የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ/007/6/12 ላይ የካቲት 27/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ተሽረዋል፡፡

2. የጋምቤላ ከተማ አስተዳደር ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍ/መ/ቁ/20105 ላይ ሚያዝያ 16/2012 ዓ.ም የሰጠው ውሳኔ በውጤት ደረጃ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

## ትዕዛዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ማ/አ

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም